የሰ/መ/ ቁ.13335

ግንቦት 25 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ በቀለ ባንጃው ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ገብሬ ታፈነ

2. ወ/ሮ ታደለች ታፈነ ቀርባለች

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

አመልካች በ3/2/96 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በ28/8/95 ዓ.ም በዋለው ችሎት በመ.ቁ.320/95 በሰጠውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 883/95 በ2/2/96 ዓ.ም በዋለው ችሎት ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ስህተቱ በዚህ ችሎት እንዲታረም ጠይቀዋል ፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው ተጠሪዎች በኦሮሚያ ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ ሲሆን በዚህም አባታችን ትቶ የሞተው በሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 288 የሆነውን የመኖሪያ ቤት ግምቱ ብር 10¸000& ኪራይ ብር 200 የ21 ወራት ብር 4¸200& የባንክ ወለድ 9%& ቡሬ በሬ ግምቱ ብር 1¸000& አንድ በርማል ግምቱ ብር 50& ሁለት ምንጀሎች ግምታቸው ብር 50& የበሬ ኪራይ ብር 1000 በአጠቃላይ ብር 5700 ከወጪ ጋር ያለውን አመልካች ይዞ እየተጠቀመበት ሲሆን እኛ የአባታችን ወራሾት መሆናችንን ያረጋገጥን በመሆኑ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍል ይታዘዝልን ሲሉ ጠይቀዋል ፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ የተጠቀሱት ንብረት የባለቤቴ የነበረ ሲሆን ባለቤቴ ሞታለች እኔም የልጆቿን ወራሽነት አረጋግጬአለሁ& ንብረቶቹ በይዞታዬ ሊገኙ

የቻሉት የተጠሪዎች እና የባለቤቱ አባት የሆኑት አቶ ታፈና ሲሳይ በተውላት ኑዛዜ መሠረት በመሆኑ የተጠሪዎች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል፡ ተጠሪዎች የተለዩ ንብረቶች እና በሬዎችን አስመልክቶ ያቀረቡት ጥያቄ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ለአመልካች ሚስት ተደረገ የተባለው ኑዛዜ በፍ/ቤት ውድቅ ሆኗል፡ በመሆኑም መብታቸውን በዚህ ኑዛዜ ላይ ሊመሰርቱ አይችሉም፡ ሆኖም ኑዛዜ በሌለበት ሁኔታ ውርስ በሕግ ወራሾች መሀል የሚካሄድ በመሆኑ እንዲሁም ተጠሪዎች እና የአመልካች ባለቤት የሟች ወራሾች በመሆናቸው ቤቱ ላይ እኩል መብት አላቸው፡ ስለዚህ አመልካች ቤቱን ከተጠሪዎች ጋር እኩል ይካፈሉ፡ አሊያም ከቤቱ ግምት የተጠሪዎችን ድርሻ ሊሰጡ ይገባል፡ ንብረቶችን በተመለከተ ማስረጃ ያልቀረበባቸው በመሆኑ ክስ ውድቅ ሆኗል ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው፡ ፍ/ቤቱም ቤቱ እንዲካፈል ባልቀረበ ክርክር ላይ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም፡ የቤቱን ኪራይ በሚመለከት አመልካች ያልካደው ነገር በመሆኑ ብር 4200 ሊከፍል ይገባል፡ ሌሎቹንም ንብረቶች ላይ የተነሣውን ጥያቄ አመልካች ያላስተባበለ በመሆኑ ግምታቸውን ሊከፍል ይገባል፡ በአጠቃላይ አመልካች ቤቱን እና ብር 5300 ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት አቤቱታውን ለክልሉ በሰር ሰሚ ችሎት አቅርቦ፡ ችሎቱም የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውን የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ኑዛዜው ፈርሷል መባሉ አላግባብ ነው፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.5 መሠረት ቀድሞ በውሣኔ ያላቀውን የወራሽነት ጉዳይ ዳግም መታየት ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተሰጠው ባግባቡ ነው ተብሎ እንሠናበት ብለዋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን ከተገቢ ሕግ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ በዚህም ተጠሪዎች በአመልካች ልጆች ይዞታ ሥር የሚገኘውን ቤት እና የቤት ኪራይን ጨምሮ ሌሎች ንብረቶችን ዋጋ እንዲረከቡ

መወሠኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው በጉዳዩ ምላሽ የሚያሻው ጭብጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ ቁ 842 እና ተከታዩቹ መሠረት ሟቹ ኑዛዜ ያልተወ በሆነ ጊዜ ንብረቱ በሙሉ ለሕጋዊ (ዘመዶች) ወራሾች እንደሚሰጥና እነዚህም ወራሾች ንብረቱ እኩል ሊካፈሉ እንደሚገባ ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ የአመልካች ባለቤት እና ተጠሪዎች የሟች የአቶ ታፈና ሲሳይ ሕጋዊ ወራሾች (ዘመዶች) መሆናቸው በተከራካሪዎች የታመነ ሲሆን አመልካችም በንብረቱ ላይ ለባለቤቴ ሙሉ መብት ይሠጣል ያሉት ኑዛዜ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የአመልካች ልጆች የእናታቸውን ድርሻ ከተጠሪዎች ጋር እኩል ሊካፈሉ ይገባል ማለት ነው ፡፡

ይህ በሆነበት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ አልቀረበም በሚል ምክንያት ቤቱን እና የቤት ኪራይን ጨምሮ የሌሎቹን ንብረቶች ግምት ተጠሪዎች ለብቻቸው እንዲወስዱ ወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት አመልካች መብት ሳይኖራቸው ንብረታችንን ይዘው ይገኛሉ በሚል ሲሆን የሥር ፍ/ቤትም ለምን የአመልካች ልጆች በተጠቀሱት ንብረቶች ላይ መብት እንዳላቸው ወስኗል፡፡ ይህ ደግሞ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ እንዳለው ባልተጠየቀ ዳኝነት የተሰጠ ውሣኔ አይደለም ፡፡

ሆኖም ከላይ እንደተገለፀው የአመልካች ልጆች ከአከራካሪው ቤት ሊያገኙ የሚገባቸው አንድ ሦስተኛውን ብቻ በመሆኑ ቤቱን ለመያዝ ከፈለጉ የቤቱን ዋጋ ሁለት ሦስተኛውን ለተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል& ሁለቱ በዚህ ካልተስማሙ ቤቱ ተሸጦ የተጠቀሰውን መጠን ለተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል ሲል ይኽ ችሎት ወስኗል፡፡ በዚህም አቤቱታ የቀረበበትን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የኦሮሚያ ምሥራት ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል ይፃፍ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት